*<u>በውጭ አገር ከምንኖር፣ ለአገራችን ቅን አሳቢ ነን  ከምንል ዜጎች ምን ይጠበቅብናል።</u>*

*በተለያየ ቦታና አጋጣሚ ኢትዮጵያውያን ተገናኝተን ማውጋት ስንጀመር በተጀመረው አርእስትላይ ብዙም ሳንወያይ ወጋችን አርእስቱን ለቆ ወደአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲለወጥና የጋሉ የሃሳባ ልውውጦች ቁጭትና ብስጭት የተሞላባቸው ስለ አገር መቆርቆር፣ ሰላለው መንግስትነኝ ባይ ሐይል በየበኩላችን የሰማነውንና ጥላቻችን በሰፊው አንዱ ካንዱ እየተቀባበልን ለረጅም ሰአታት ተወያይትን መበታተኛ ሰአታችን ሲደር ውይይታችን ቁጭታእን ፈርና እልባት ሳይዝ፣ በሉ እንግዲህ ምንታደርጉታለችሁ? ተባብለን የምንለያየው አንዴና ሁለቴ ብቻ አይደለም። እንገዲህ ከላይ ላጭሩ ለመጠቆም የተፈለገው ለአገራችን ቅን የምናስብ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ አጋጣሚዎችና ቦታዎች ሊያገናኙን እንደሚችሉ፣ ከተገናኘንም በሌላ ጉዳዮች ከመወያየት ይልቅ በአገራችን ጉዳይላይ መወያየቱንና ኢንፎርሜሽን መለዋወጡን እንደምናዘወትር፣ ነገር ግን ከዚህ አልፈን ተግባራዊ ማድረግ ያለብንን ጉዳይ ቸል ብለን እንደምናልፈውና ለጉዳዩ ሁላችንም እኩል ሓላፊነት እንዳለብን አውቀን እንደምንዘነጋው ነው።*

*እኛ በውጭ አገር የምንኖርና አገራችንን የምንወድ የሰው አገር ኑሮ በተለያየ መለኩ የሰለቸን፣ አገራችን እንዳንመለስ የተለያዩ ችግሮች ቢኖሩብንም፣ ነገር ግን ዋነኛው ጋሬጣ የሆነብን አገራችን ያለችበት ሁኔታ እንደሆነ ጠንቅቀን የምናውቀው ጉዳይ እንደሆነ ሁላችንም የምንተማመንበት ነው። ሁላችንም በአንድ መስመርም መሰለፋችንን የሚገልጹ ሁኔታውችን በተለያየ መልኩ ሁላችንም ስለአገር ጉዳይ ስንወያይ ከምንሰነዝረው ሃሳብና ከምናሳየው ዜግነታዊ ቁጭት ማየት የምንችለው ሃቅ ነው። ሁላችንም አንድ ከሚያደርጉን ዋናዋና ነጥቦች፣ ለአገራችን የምንቆሮቆር፣ በሰው አገር የምንኖርና ወደአገራችን ለመመለስ የምንጓጓና የምንናፍቅ፣ አገራችን በአስከፊ ስርአት ውስጥ እንደወደቀችና ከዚህም መውጣት እንዳለባት የምናምን፣ እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የሚደረጉትን ትግሎችና እንቅሰቃሴዎች በተለያየ መልኩ የምንደግፍ እንደሆኑ ያለጥርጥር የምንስማማባቸው እውነቶች ናቸው።*

*ታድያ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሁነተዎችና እውነቶች የምንስማማ ከሆንን ፍላጎታችንን እውነት ለማድረግ ተግባራዊ መሆን ለምን አቃተን? ወይንም ለምን አልፈለግንም? እዚህላይ እነዚህን ጥያቄዎች በተለያየ መልኩ መመለስ ቢቻልም፣ በአሁኑ ወቅት ያሉብንን ልዩነቶችና ጥርጣሬዎች ወደጎን ትተን በአንድ መስመር ተሰልፈን የተቀጣጠለቀወን ትግል አፋፋሚ መሆን እንዳለብን የሚያስገድዱን የምንስማማባቸውና አንድ የሚያደርጉን ሁኔታዎች በርካታ ሰለሆኑ እነሱላይ በማተኮር እኛ በውጭ አገር የምንኖርና ለአገራችን ቅን የምናስብ ኢትዮጵያውያን የትግሉን ግብ ለማፋጠን ዋነኛ አጋር መሆናችንን ሳንዘነጋ የሚጠበቅብንን የሞራል፣ የቁሳቁስ፣ እንዲሁም በዋነኛነት አስፈላጊ በሆነው የገንዘብ እርዳታ በማድረግ በተገናኘን ቁጥር በቁጭትና በብስጭት ከተወያየን በህዋላ ምንታድጉታለችሁ ተባብለን ከመለያየት ባሻገር የሚጠበቅብንን ታላቅ ሃላፊነት ብንወጣን ለአገራቸው ቁምነገር ሠሩ ከሚባሉት ዜጎች አንዶቹ እንደምንሆንና ለግል ሞራላችንም ታለቅ አስተዋጽዎ ሊኖረው ስለሚችል በተለየዩ አጋጣሚዎች በተገናኘን ቁጥር መወያየታችንና ኢንፎረሜሽን መለዋወጣችን እንዳለ ሆኖ፣ ነገር ግን <u>ምንታደርጉታለችሁ</u> ተባብለን ከመለያየት ይልቅ ለውይይታችን እልባት በመስጠት ሁኔታዎችን ተግባራዊ የምናደርግበትንም ጨምሮ በመወያየት አገራች ካለችበት መከራ እንድትላቀቅንና የሁላችንም ወደ አገር መመለስንም እውን ለማድረግ መረባረብ እንዳለብንና፣ የተቀጣጠለውን የሕዝብ አመፅ ለማፋፋም ታላቅ ሀላፊነት እንደሚጠበቅብን ለሁላችንም የታወቀ ጉዳይ ቢሆንም ደጋግሞ ማሳሰቡም አስፈለጊነቱ በእኔ እይታ ጠቃሚነት እንዳለው በማመን የህችን አጬር ቅስቀሳ ለራሴም ሆነ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያጋጠሙኝን ሁኔታዎ መነሻ በማድረግ ለብዙሃኑ እንዲደርስና አስተዋጽአችንን ለሚታወቁና በሰፊው ለሚንቀሳቀሱ ፀረ ወያኔ የሆኑ ትግሎችና እንቅስቃሴዎች ዛሬ ነገ ሳንል ማገዝ ዜግነታዊ ግዴታችን ነውና እንነሳ እላለሁ ።*

BAW   FRANKFURT